

***ጋዜጣዊ መግለጫ***


ለተጨማሪ መረጃ ቀጥሎ በተመለከተው

የአሜሪካ ኤምባሲ፤

ቁጥር ይደውሉ፡-011-130-7033

አዲስ አበባ፤ኢትዮጵያ

ድረገጽ፡- http://ethiopia.usembassy.gov


---

**3ኛው ዓለም አቀፍ የቡና ኮንፈረንስ በጥራት ደረጃ እና በወጪ ንግድ ገበያ የምርት መገኛ መለየት ላይ ያተኩራል**

**አሜሪካ የኢትዮጵያ ቡና ላኪዎች ማኅበር ከጥቅምት 26-27 በአዲስ አበባ የሚካሄደውን ዓለም አቀፍ የቡና ኮንፈረንስ እንዲያስተናግድ ድጋፍ አደረገች**

አዲስ አበባ፤ኢትዮጵያ፤ጥቅምት 26 ቀን 2007 ዓ.ም.፡-የአሜሪካ መንግሥት በቡና አምራች ኢንዱስትሪ ውስጥ ከሚገኙ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የኢትዮጵያ ቡና ላኪዎች ማኅበር 3ኛውን ዓለም አቀፍ የቡና ኮንፈረንስ እንዲያስተናግድ ድጋፍ አደረገ፡፡ የቡናን የእሴት ሰንሰለት ማጠናከር የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ የግብርና ዕድገት መርሀ ግብር አካል የሆነው የግብርና ምርት ገበያ ልማት ፕሮጀክት ዋንኛ ትኩረት ሲሆን፤ፕሮጀክቱ ለድርጅቱም ሆነ የንግድ ጉባኤውን በማስተዋወቅ ረገድ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

የኢፌዲሪ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ፣በኢትዮጵያ የአሜሪካ ምክትል አምባሳደር ሚስተር ፒተር ቭሩማን፣የዓለም አቀፉ የቡና ድርጅት ዋና ዳይሬክተር ሮቤሪዮ ኦሊቬራ ሲልቫ እና የአሜሪካ ልዩ ቡና ማኅበር ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሪክ ራይንሃርት “ለጥራትና ለምርት መገኛ መለየት” በሚል መፈክር የተከበረውንና በኢትዮጵያና በዓለም አቀፍ ደረጃ የተመዘገቡ ከ300 በላይ የሚሆኑ ተሳታፊዎች የተካፈሉበትን የዛሬውን 3ኛውን ዓለም አቀፍ የቡና ኮንፈረንስ በጋራ ከፍተዋል፡፡

እስታርባክስ የቡና ኩባኒያ፣ኔስሌ ኔስካፌ ዶልቼ ጉስቶ፣ሞንዴሌዝ ኢንተርናሽናል እና ሚድሮክ-ኢትዮጵያን የመሳሰሉ የዘርፉ ግንባር ቀደም ተዋናዮች የንግድ ዕድሎችን በሚመለከት አዳዲስ ምልከታዎችን አቅርበዋል፡፡ ኮንፈረንሱ በየዓመቱ የሚካሄድ ሲሆን በብቃት ማረጋገጫ ዙሪያ ያሉ ዕድሎችና የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን፣የዘረመል የትኩረት አቅጣጫዎችን፣እንዲሁም በጥራት ማሻሻል፣ ልዩ የኢትዮጵያ ቅርስ በሆኑ የተለያዩ የቡና ዓይነቶች፣ በኢትዮጵያ ቀጣይነት ባለው መልኩ የቡና ዘርፉን በማስፋፋትና በሀገሪቱ የሚገኙ አነስተኛ ወንድና ሴት አምራቾችና የዘርፉ ሠራተኞች ትርፋማ በሚሆኑበት መንገድ ዙሪያ ይመክራል፡፡

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ በቀጣይ ለቡና ላኪዎች ይፋ የሚሆን የምርት መገኛ መለያ ዘዴ አቅርቧል፡፡ የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ ጥምረት የታየበት ይኸው የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የምርት መገኛ መለያ ጥረት በኢትዮጵያ በሚገኘው የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ በሚመራው መጪውን ትውልድ መመገብ የተሰኘ መርሀ ግብር የ1.5 ሚሊዮን ዶላር የገንዘብ ድጋፍ የተደረገለት ሲሆን፤ኔስል፣ሞንዴልዝና ኤዲኤች የተሰኘ የኔዘርላንድ ፋውንዴሽን በጋራ 900,000 ዶላር አበርክተዋል፡፡

በኮንፈረንሱ መክፈቻ ላይ በኢትዮጵያ የአሜሪካ ምክትል አምባሳደር ፒተር ቭሩማን የቡና ዘርፉ ለኢትዮጵያ ልማትና ዕድገት ስለሚኖረው አስተዋፅዖ ሲናገሩ፡-“የኢትዮጵያ የቡና ወጪ ንግድ እምቅና ገና ያልተነካ ሲሆን የአሜሪካ መንግሥት አሜሪካን ጨምሮ በተለያዩ ሀገራት የሚገኙ አዳዲስ ገበያዎችን፣ የግሉ ዘርፍ ሽሪኮችንና ባለሀብቶችን የማፈላለግ ሥራ በመሥራት ላይ ይገኛል፤ባለን ጣምራ ዓላማም በኢትዮጵያ የቡናው ዘርፍ እንዲስፋፋ ብቻ ሳሆን በርካታ አነስተኛ የቡና አምራቾችና ቤተሰቦቻቸው ተጠቃሚ ሆነው ማየት እንፈልጋለን” ብለዋል፡፡